# ትራንስፖርት ባለስልጣን

“በእግረኞች የመንገድ አጠቃቀም ላይ የተጣሉትን ቅጣቶች”

ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 693/2013

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የመንገድ ትራፊክ አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በተለይ የእግረኞች ተጋላጭነትን አስከፊ በመሆኑ ይህንን ለመቆጣጠር እና ስርዓት ለማስያዝ የትራንስፖርት ባለስልጣን በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ይህን ጥረት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ እግረኞች በመንገድ ላይ ሲንቀሳቀሱ የትራፊክ ደንቦችን አክብረው የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ በህግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 395/2009 ተሻሽሎ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

በተሻሻለው የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ መሰረት የትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም በህግ ስልጣን የተሰጠው ሌላ ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችን የተላለፈ እግረኛ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰው ላጠፋው ጥፋት የሚገባውን ቅጣት እንዲፈጽም የቅጣት ወረቀት ይሰጠዋል በሚለው መሰረት ዝርዝር አፈጻጸሙን ለተገልጋዩና ለፈጻሚው በመመሪያ ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ በሚንስትሮች ደንብ ቁጥር 395/2009 አንቀጽ16 ንዑስ ቁጥር 3 መሰረት የእግረኞችን የመንገድ አጠቃቀም በሚመለከት ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቷል፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ
የሬከርድና ማህደር አገልግሎት

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የእግረኞች የቅጣት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 693/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ በመንገድ ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208 /2003 እና የተሻሻለው ደንብ ቁጥር 395/2009 የተሰጡት ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

1. "ህግ አስከባሪ"ማለት ደህንነቱ የተጠበቀ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር በመንገድ ላይ ተሽከርካሪን ለመቆጣጠር ስልጣን ያለውና ጸጥታን ለማስከበር የተሰማራ ማንኛውም ህግ አስከባሪ ማለት ነው፡
2. "ደንብ" ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 395/2009 ማለት ነው
3. "የትራፊክ ደንብ አስከባሪ አካል" ማለት የመንግስት ህጎችን ደንቦችን ጥሰት ለመከላከልና ለመቆጣጠር አግባብ ባለው ሕግ የተቋቋመ ወይም ውክልና የተሰጠው ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ሲሆን ደንብ የሚያስከብሩ የክልል የመስተዳደሮችን፣ መዘጋጃ ቤቶች ፣የደንብ ማስከበር ጽ/ቤቶች፣ የትራንስፖርት ቢሮዎችን፣ የፖሊስ ተቋማት አደረጃጀቶችን ያካትታል፡፡
4. "የትራፊክ ደንብ አስከባሪ" ማለት በደንብ ቁጥር 395/2009 የእግረኞችንና ሌሎች የትራፊክ ደንብ ጥሰቶችን የሚከላከልና የሚቆጣጠር ሆኖ ደንብ ለማስከበር ህጋዊ ስልጣን ከተሰጠው አካል የተመደበ ወይም የተቀጠረ ሰው ወይም ትራፊክ ተቆጣጣሪ ነው፡፡
5. "የተሽከርካሪ መንገድ ማለት" ለተሽከርካሪዎች መተላለፊያ ተብሎ የተሰራ መንገድ ሲሆን ባለአንድ ወይም ባለሁለት አቅጣጫ መተላለፊያ ያካትታል፡፡
6. "የእግረኛ መንገድ ማለት" እግረኞች እንዲተላለፉበት ተብሎ የተሰራ መንገድ ነው፣

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

7. “የጋሪ መንገድ ማለት" ጋሪዎች ከሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ጋር በጋራ እንዲጠቀሙበት በሚመለከተው አካል የተለየ መንገድ ሲሆን የጋራ ማቋረጫዎችንም ያካትታል፡፡

8. "የብስክሌት መንገድ ማለት“ ለብስክሌት ተጠቃሚዎች ብቻ መተላለፊያ እንዲሆን የተሰራ መንገድ ማለት ነው፡፡

9. “ማህበራዊ አገልግሎት” ማለት ጥፋት በተፈጸመበት መንገድ ወይም አከባቢ ከጽዳትና ውበት ስራዎች እንዲሁም ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት ጋር የተገናኙ ተግባራት ማከናወን ማለት ነው፡፡

10. “አካል ጉዳተኛ” የሚለው በተፈጥሮ ህመም ወይም በማናቸውም አደጋ ምክንያት ለዘለቄታው የአካል ጉዳት የደረሰበትን የህብረተሰብ ክፍል ያጠቃልላል፡፡

11. “ተመጣጣኝ የሆነ የማህበራዊ አገልግሎት” ማለት እንደየ ቅጣቱ ክብደት እና እድሜ እና ጤንነት ሁኔታ የአትክልት ቦታ መኮትኮት ፣ውሃ ማጠጣትና መቆፈር፣የአከባቢ ጽዳት ስራ መስራት ፣በመንገድ ዳር የሚገኙ አላስፈላጊ ቁጥቋጦ መቁረጥ፣ መንገድ ማጽዳት፣የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ለማረጋገጥ እግረኞች በግራ ጠርዝ እንዲጓዙ ፣በእግረኛ መሻገሪያ ድልድይ እንዲጠቀሙ እንዲሁም በዜብራ መስመር እንዲሻገሩ የማስተባበር ስራ ማለት ነው፡፡

12. "ሰው“ማለት በተፈጥሮ ሰው የሆነ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

13. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>አላማ</u>

በመንገድ ላይ ደህንነቱ የተጠበቀ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማረጋገጥና የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር ተሻሽሎ በወጣው የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 395/2009 የእግረኞች የቅጣት አፈጻጸም ድንጋጌ በግልጽ እና ወጥ በሆነ መንገድ ተፈጻሚ ለማድረግ ነው፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በኢትዮጵያ መንገዶች በሚያስተዳድረው እና በከተማ አስተዳደር በሚገኙ መንገዶች በሚጠቀሙ እግረኞች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተለያዩ አካላት ኃላፊነትና ተግባር

## 5. የትራንስፖርት ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 እና ተሻሽሎ በወጣው 395/2009 እና በሌላም ሕግ የተሰጠው ኃላፊነትና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የሚከተሉት ኃላፊነት እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ይህ መመሪያ በስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡
2. በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል፡፡
3. ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን ያከናውናል ፡፡
4. የእግረኞችን የአፈጻጸም መመሪያን በሚመለከት ከክልሎች ጋር እርስ በርስ የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት ሥርአት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡
5. የዚህ መመሪያ አስፈፃሚ አካል መመሪያውን በሚያስፈጽምበት ወቅት ያጋጠመውን ችግር በመረጃ አስደግፎ ሲያቀርብ ፈጣን ምለሽ ይሰጣል፡፡
6. በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 እና በማሻሻያው ድንብ ቁጥር 395/2009 እንዲያስፈፅሙ ሥልጣን ከተሰጣቸው አስፈፃሚ አካል ውጭ ይህንን መመሪያ የሚያስፈጽምና ድጋፍ ለሚያደርግ ሌላ አካልን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
7. የእግራኛ ቅጣት መረጃ ማሰበሰቢያ ቅጽ ያዘጋጀል በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት መረጃዎች ማሰባሰባቸውን ይከታተላል ፤ይቆጣጠራል፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ
የሬከርድና ማህደር አገልግሎት

6. <u>የክልልና ከተማ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌላ ህግ የተሰጣቸው ተግባር እና ሀላፊነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የሚከተለውን ዝርዝር ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

1. ይህ መመሪያ በክልላቸው ወይም በከተማቸውበስራ ላይ እንዲውል በከተማ እና ከከተማ ውጪ በአግባቡ በስራላይ መዋሉን ያረጋግጣሉ፡፡
2. መመሪያውን ለማስፈጸም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለእግረኞች ምቹ መንቀሳቀሻ ቦታዎች ፡ በእግረኛ ማቋረጫ ላይ የእግረኛ መለያ አጥሮች ፡ምልክትና ማመላከቻዎች መሟላታቸውን የማረጋገጥ እና እንዲሟሉ የማድረግ ተግባራትን በማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን መንገዶች ይለያሉ፡፡
3. የመንገዶችን የአደጋ ሁኔታ በመገምገም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን መንገዶች በመለየት በሂደትም የጋራ እቅድ በማውጣት መመሪያው በሁሉም የአካባቢው መንገዶች ላይ እንዲተገበር ያደርጋሉ ፡፡
4. በመንገድ ላይ የሚካሄዱ ለትራፊክ ፍሰት የሚያውኩ አደገኛ ቦታ ላይ ያሉ የንግድ ቦታዎች ፣ትምህርት ቤቶችና ፋብሪካዎች መውጫና መግቢያ ለአደጋ አጋላጭ አለመሆናቸው ማረጋገጥና የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

7. <u>የፖሊስ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌላ ህግ የተሰጣቸው ተግባር እና ሀላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የሚከተለውን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናሉ፡-

1. የእግረኞች የመንገድ አጠቃቀም በሚመለከት አጠቃላይ እንቅስቃሴው ደህንነቱንና ሰላሙ የተጠበቀ እንዲሆን ይከታተላል ይደግፋሉ፡፡
2. ከደንብ አስከባሪ አካላት አቅም በላይ በሆኑ የደንብ ተላላፊዎች ላይ ለህግ በማቅረብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡
3. የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋሉ፡፡

ከማህሌት ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

8.- <u>ደንብ ለማስከበር የተቋቋሙ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌላ ህግ የተሰጣቸው ተግባር እና ሀላፊነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የሚከተለውን ዝርዝር ተግባራቶችን ያከናውናሉ፡-

1) ከትራንስፖርት ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት ደህንነቱ የተጠበቀ የእግረኞች መተላለፊያ፣ የእግረኞች መለያ አጥር ፣ የማቋረጫ ምልክቶችና ማመላከቻዎች እንዲሟሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አለባቸው ፡፡
2) .ቁጥጥር የሚደረግባቸው መንገዶችን ከትራንስፖርት ቢሮዎች ጋር በመሆን መሟላት የሚገባቸውን በሟሟላት በቅደም ተከተል የመለየትና በሂደትም በመንገዶች ላይ ሙሉ በሙሉ ደንቡ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው፡፡
3) ደንብ ተላላፊዎች ከመቀጣታቸውም በፊትም ሆነ ቅጣቱ ከተፈጸመ በኋላ ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡
4) በደንብ ተላላፊዎች የሚፈፀምባቸውን የክፍያ አፈፃፀም ሁኔታ ለህብረተሰቡ በግልጽ ያስውቃሉ፡፡
5) ክፍያ መፈጸም የማይችሉ እግረኞች ወይም ግለሰቦች ማህበራዊ ስራ የሚያከናውኑበት ተግባራት በቅድሚያ ለይቶ በማዘጋጀት ደንብ ተላላፊዎቹ እንዲሰማሩ ያደርጋሉ፡፡
6) ጥፋት የፈጸመውን እግረኛ ሙሉ መረጃ ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት መያዝ አለባቸው፡፡
7) ጥፋት የፈጸመ እግረኛ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ሲደረግ ደንብ አስፈጻሚው የማህበራዊ አገልግሎት ለመፈጸሙ የማረጋገጫ ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
8) በመመሪያው መሰረት ክፍያውን የተቀበለው ደንብ አስከባሪው ህጋዊ ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት አለበት ፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

9. የክልልና ከተማ መስተዳድር የመንገድ የመሰረተ ልማት የሚያስተዳድሩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

በሌላ ህግ የተሰጣቸው ተግባር እና ሀላፊነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራቶች ያከናውናሉ፡፡

1. የእግረኞች ማቋረጫ መንገዶች ለእግረኞች ምቹ እንዲሆን ማድረግ
2. በእግረኞች መንገድ ላይ ግኡዝ አካላት ማንሳት፣ ተረፈ ምርት እና የኮንስትራክሽን ቁሳቁሶች እንዲሁም ሌሎች የእግረኛ የመንገድ አጠቃቀም የሚያውኩ ቁሳቁሶች እንዲወገዱ ማድረግ
3. ለእግረኞች መንገድ አጠቃቀም የሚረዱ ምልክትና ማመላከቻዎች እንዲሁም የመንገድ መብራቶች እንዲሟሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል ፡፡

10. የእግረኞች ኃላፊነትና ግዴታ

በአገሪቱ ላይ የሚጠቀም ማንኛውም እግረኛ የሚከተለው ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

1. አረጋዊያንና ህጻናት እንዲሁም ከአካል ጉዳተኞች የገንዘብ ቅጣት መክፈል ከልቻሉ የማህረበራዊ አገልግሎት መስጠት ሳይገደዱ ለ15 ደቂቃ ግንዘቤ በማውሰድ መሄድ ይችላሉ፡፡
2. ጥፋት የፈጸሙ እግራኞች እንደጥፋታቸው በደንቡ ላይ የተቀመጠውን ክፍያ ወድያውኑ በአካባቢው ለሚገኘው ደንብ አስከባሪ መፈጸም አለባቸው፡
3. ጥፋት የፈጸመው እግራኛ በደንቡ ላይ የተጣለበትን የቅጣት ክፍያ ወይም በዚህ መመሪያ የተደነገገውን ማህበራዊ አገልግሎት መፈጸም አለባቸው፡፡
4. ደንብ ቁጥር 395/2009 እና ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የተሰማሩ አካላት በማንኛውም ሁኔታ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ማክበር አለባቸው፡፡
5. በደንብ ቁጥር 395/2009 ሠንጠረዥ ለ ተራ ቁጥር 4 ላይ የተደነገገው ለእግረኞች የተከለከለውን የጥፋት ዝርዝሮች መፈፀም የለባቸውም፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

11. የመንገድ ትራፊክ በጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሠጡ አካላት ሀላፊነት እና ተግባር፡-

1. ለእግረኞችና ለሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ደንቡን እንዲያከብሩ የማስተባበር እና ግንዛቤ መስጠት
2. ማናቸውም የትራፊክ ህግ ጥሰቶች ሲያገጥማቸው ለሚመለከታቸው መረጃ መስጠትና የሰጡትን መረጃ ውጤት የማወቅ፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ቅጣት

12. የቅጣት አፈጸፀም

1. በደንብ ቁጥር 395/2009 የትራፊክ ተቆጣጣሪ በተጨማሪ ከባለሥልጣኑ ውክልና ያገኘ ማንኛውም ሕግ አስከባሪ ወይም ደንብ አስከባሪ የዚህ መመሪያ አስፈጻሚ ናቸው፡፡
2. ጥፋት ፈጽሞ ቅጣት የተጣለበት እግረኛ የቅጣት ክፍያውን የደንብ ማስከበር ገንዘብ መሰብሰቢያ ስርዓት መሰረት ክፍያ ይፈጽማል፡፡
3. በደንቡ ወይም በዚሁ መመሪያ ስልጣን የተሰጠው አስፈፃሚ በደንቡና በዚህ መመሪያ የተጠቀሰውን ጥፋት ለፈፀመ ማንኛውም እግረኛ የቅጣት ፓድ ወይም ደረሰኝ በመያዝ ላጠፋው ጥፋት የደንብ አስከባሪው አካል የቅጣት ደረሰኝ ይሰጠዋል፡፡
4. ደንብ አስከባሪው እያንዳንዱ እግረኛ ደንብ በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ በሚገኝበት ወቅት የቅጣት ክፍያ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡
5. የተጣለበትን ቅጣት ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆነ እግረኛ ላይ ደንብ አስከባሪው ከትራፊክ ወይም ከመደበኛ ፖሊስ ጋር በመተባበር ቅጣቱን እንዲቀበል ያስገድዳል፡፡
6. ከ14 አመት በታች የሆኑ ተማሪዎች በደንቡ ላይ የተቀመጠውን የትራፊክ ህግ ተላልፈው ሲገኙ በደንቡ ላይ የተቀመጠውን ክፍያ መክፈል ካልቻሉ አስፈፃሚው አካል የሚማሩበትን ት/ቤት በማጣራት በሪከርድነት ይዞ ለየት/ቤታቸው በማስተላለፍ በትራፊክ ክበባት አማካይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

ካሳሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

7. ከአስራ አራት አመት በታች እና ተማሪ ያልሆኑ ህጻናት ፡ አዛውንቶች፣ ነፍሰ ጡሮችና የአካል ጉዳተኞች በህጉ ላይ የተቀመጠውን የትራፊክ ደንብ ተላልፈው ሲገኙ አሰፈፃሚው አካል ምክርና ትምህርት በመስጠት በድጋሚ ስህተት እንዳይፈጽሙ ማስጠንቀቅያ በመስጠት እንዲለቀቁ ያደርጋል፡፡

8. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል አዛውንት ማለት ዕድሜአቸው ከ60 ዓመት በታች የሆኑትን አያካትትም፡፡

9. ይህ መመሪያ በተግባር ላይ እንዲውል  አገልግሎት የሚሰጡ  ትራፊክ አስተባባሪዎችን ትዕዛዝ ባለመቀበልና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመዝለፍና በመምታት ተጽዕኖ የሚፈጥር ግለሰብ በደንብ አስከባሪና በጸጥታ አስከባሪዎች አማካኝነት በወንጀል ክስ እንዲመሠረትበት  ያደረጋሉ፡፡

10. ጥፋቱን የፈፀመው እግረኛ በደንቡ ላይ የተጣለበትን የቅጣት ክፍያ ወይም በዚህ መመሪያ የተደነገገውን ማህበራዊ አገልግሎት ለመፈጸም ፍቃደኛ ካልሆነ እና ከህግ አስከባሪዎች ጋር አምባጋሮ የሚፈጥር እግረኛ በጸጥታ አስከባሪዎች በደንብ መተላለፍ እና በወንጀል ክስ ይመሰረትበታል፡፡

11. ሰማንያ ብር የሚያስቀጠውን ጥፋት የፈጸመ እግረኛ የገንዘብ ቅጣቱን መክፈል ያልቻለ እንደሆነ ለ 1 /አንድ/ ሰአት የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

12. አርባ ብር የሚያስቀጠውን ጥፋት የፈጸመ እግረኛ የገንዘብ ቅጣቱን መክፈል ያልቻለ እንደሆነ ለ 30 /ለሳለሰ ደቂቃ/ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

13. በደንብ ቁጥር 395/2009 ሠንጠረዥ ለ ተ.ቁ 4 ላይ የተገለፀው ጥፋቶች በእግረኞች ሲፈፀሙ እንደ ጥፋቱ በደንቡ ላይ የተቀመጠው የገንዘብ ቅጣት ይቀጣሉ፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. **የመተባበር ግዴታ**

ይህ መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም አካል አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

14. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

የባለስልጣኑ መ/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን የአፈጻጸም መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል፡፡

15. **መመሪያውን ስለማስፈጸም**

የትራንስፖርት ባለስልጣን ይህን መመሪያ እንዲያስፈጽም ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

16. **የመመሪያው ተፈጻሚነት**

ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ከመጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም

ካሳሁን ኃ/ማርያም

የትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር